ጤና

# Open Enrollment 2022 (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን)

## ከጁላይ 1-20 ለተንከባካቢዎች እና ጥገኞቻቸው




### - በዚህ ዓመት አዲስ -
## $10 የጥርስ ህክምና
### ለጥገኞች

በወር 120 ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ ከሰሩ፣ አሁን ጥገኞችዎን በወር $10 ብቻ በመክፈል በጥርስ ህክምና ሽፋን መመዝገብ ይችላሉ*!

* ለኤጀንሲው አገልግሎት አቅራቢዎች (AP) እና CDWA የግለሰብ አቅራቢዎች (IP) ብቻ፡-

## ጁላይ 1-20፡- በዚህ ዓመት የእርስዎ ብቸኛ እድል

Open Enrollment (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን) ሽፋንዎ ላይ ለመመዝገብ ወይም አማራጭ ለውጦችን ለማድረግ አመታዊ እድልዎ ነው*።

- ✓ አሁን ብቁ ከሆኑ እና በመድን ሽፋን ከተመዘገቡ፣ የመድን ሽፋንዎ ኦገስት 1 ይጀምራል።
- ✓ አሁን ላይ ብቁ ካልሆኑ፣ አሁንም የተሟላ የጤና ጥቅሞች ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ብቁ ሲሆኑ የመድን ሽፋንዎ ይጀምራል።
- ✓ አስቀድመው የተመዘገቡ ከሆኑ፣ በመድን ሽፋንዎ ላይ ጥገኛ ማከል ወይም አማራጭ ለውጦችን ማድረግ ካልፈለጉ በስተቀር እርምጃ መውሰድ አያስፈልግዎትም።

*እርምጃ ካልወሰዱ፣ ብቁ የሆነ የህይወት ክስተት ከሌለዎት በስተቀር እስከሚቀጥለው **Open Enrollment** (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን) ድረስ ለውጦችን ማድረግ ላይችሉ ይችላሉ።

SEIU 775 BENEFITS GROUP

# ማውጫ


**የጥገኛ መድን ሽፋን** ................................ ገጽ 4

**የእኔ ዕቅድ** ............................................ ገጽ 5

ለውጦችን ያድርጉ ወይም ኦንላይን ይመዝገቡ

**የጤና እንክብካቤ ዕቅድ ዋና፣ ዋና ነጥቦች** ............................................ ገጽ 8

ስለ ጤና ዕቅድዎ ይወቁ

**ሜዲካል** ............................................ ገጽ 10

የሜዲካል ዕቅድ አጭር ማጠቃለያ

**የጥርስ ሕክምና** ................................... ገጽ 13

የጥርስ ሕክምና ዕቅድ አጭር ማጠቃለያ

**የተለመዱ የኢንሹራንስ ልዩ ቃላት** ............................................ ገጽ 18


ማስታወሻ፦ በSEIU 775 Healthcare NW Health Benefits Trust የቀረበው መድን ሽፋን አነስተኛውን አስፈላጊ ሽፋን እና ተመጣጣኝ እንክብካቤ ህግን አነስተኛውን የመጠን መድን ሽፋን ያሟላል። ይህ ማለት በSEIU 775 Healthcare NW Health Benefits Trust በኩል ለመድን ሽፋን ብቁ ከሆኑ ነገር ግን ላለመመዝገብ ከመረጡ፣ በዋሽንግተን የጤና ጥቅማ ጥቅሞች ልውውጥ ለደረሰው መድን ሽፋን ለፕሪሚየም የታክስ ክሬዲት ብቁ መሆንዎ ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።

ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎ ልውውጥን በ **1-855-923-4633** ወይም በ **wahealthplanfinder.org** ኦንላይን ያግኙ።



# መመሪያዎችና ዋና ዋና ነገሮች

የእርስዎ ፓኬት ስለ የእርስዎ ጤና መድን፣ የሕክምና እና የጥርስ ሕክምና አጭር ማጠቃለያዎች እና የተለመዱ ዓይነት የጤና ኢንሹራንስ ውሎች አንኳር የሆኑ ነጥቦችን ያካትታል። እስካሁን ካልተመዘገቡ ወይም ቀደም ብለው የተመዘገቡ ሆነው ባልዎት የመድን ዕቅድ ላይ አማራጭ ለውጦችን ያደረጉ ከሆኑ ራስዎት እና ማንኛውም ጥገኛዎችዎን ለመመዝገብ የሚያስፈልግዎትን ማመልከቻ በተጨማሪ ያገኛሉ።

**በዚህ ዓመት አዲስ!**
**$10 የጥርስ ህክምና ለጥገኛዎች**

በወር 120 ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ የሚሰሩ APs እና CDWA IPs አሁን ጥገኞቻቸውን በጥርስ ህክምና ሽፋን መመዝገብ ይችላሉ። በገጽ 4 ላይ የበለጠ ይወቁ።

## በOpen Enrollment (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን) ወቅት የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

✓ ለጤና ኢንሹራንስ ማመልከቻ ማስገባት (እስካሁን ያልተመዘገቡ ከሆኑ)።
✓ በእርስዎ የጥርስ ሕክምና መድን ላይ አማራጭ ለውጦችን ማድረግ (እስካሁን ያልተመዘገቡ ከሆኑ)።
✓ ጥገኛ ወደ ሽፋንዎ ያክሉ (APs እና CDWA IPs ብቻ)።

## የአዲስ ተመዝጋቢዎች መድን ሽፋን ኦገስት 1 ይጀምራል።

አስቀድመው የተመዘገቡ ከሆኑ፣ በመድን ሽፋንዎ ላይ አማራጭ ለውጦችን ማድረግ ካልፈለጉ በስተቀር እርምጃ መውሰድ አያስፈልግዎትም።

ለግል የጤና ሽፋን ማመልከት ከፈለጉ፡-

✓ የጤና መድን ማመልከቻውን ይሙሉት እና ያስገቡት።
✓ በወር $25 ይክፈሉ።
✓ አገልግሎቱን ለማግኘት ብቁ እንደሆኑ ለመቀጠል በወር 80 ሰዓታት ሥራ መሥራትዎን ይቀጥሉ።*
✓ በጤና እንክብካቤ መድን ሽፋንዎ ይደሰቱ!

*በብቁነት መስፈርት ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ Open Enrollment (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን) ድረገጽን በ **myseiu.be/oe2022** ላይ ይጎብኙ ወይም ኮዱን ለመቃኘት በስልክዎ ላይ ያለውን ካሜራ ይጠቀሙ።

# እንዴት መመዝገብ ወይም ለውጦችን ማድረግ እንደሚቻል

## ማመልከቻዎ እንዲስተናገድ እስከ ጁላይ 20 ድረስ መግባት አለበት።

### ኦንላይን

Health: My Planን በመጠቀም እስከ ጁላይ 20 ድረስ የኦንላይን ማመልከቻ ይሙሉ። ኮዱን ለመቃኘት በስልክዎ ላይ ያለውን ካሜራ ይጠቀሙ ወይም የበለጠ ለመረዳት **myseiu.be/oe-myplan-22** ን ይጎብኙ።

### መልዕክት ወይም ፋክስ

በጤና መድን ጥቅማ ጥቅም ማመልከቻ ላይ ወደ ተዘረዘረው አድራሻ የእርስዎን ማመልከቻ እስከ ጁላይ 20 ይላኩ። የአሜሪካ ፖስታ አገልግሎትን መጠቀም ግዴታ ነው። ወይም ፋክስ ወደ 516-723-7395 ይላኩ።

# የጥገኛ መድን ሽፋን




– በዚህ ዓመት አዲስ –

**$10 የጥርስ ህክምና**

ለጥገኞች

**120** ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ ከሰሩ፣ ለ **$10** የጥርስ ህክምና መድን ሽፋን ለጥገኞችዎ ብቁ ነዎት! በጁላይ **1-20** መካከል ያመልክቱ።

- ብቁነትዎ የሚወሰነው በወር ምን ያህል ሰዓት እንደሚሰሩ ቢሆንም የ80 ሰዓት ምርጫን ወይም የ120 ሰዓት ምርጫን መምረጥ ይችላሉ። ለእርስዎ እና ለጥገኞችዎ የመድን ሽፋን የሚጀምረው እርስዎ ብቁ ሲሆኑ ነው።
- ወርሃዊ ክፍያዎ ካልደረሰ ወይም የስራ ሰዓትዎ ከሚፈለገው በታች ከቀነሰ፣ ጥገኞችዎ ሽፋን ያጣሉ።

## ከ 2 ጥገኛ መድን ሽፋን አማራጮች ውስጥ ይምረጡ።

### የ80 ሰዓት ምርጫ:-

በወር ከ**80-119** ሰዓታት ለሚሰሩ ተንከባካቢዎች በጣም የተሻለ። በወር 80 ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ እስኪሰሩ ድረስ የጥገኛዎ መድን ሽፋን አይጀምርም።

- ሙሉ የህክምና እና የጥርስ ህክምና በሙሉ ፕሪሚየም ወጪ (በወር $686-$786፣ እና ለመድን ሽፋንዎ $25 በወር)።

### የ120 ሰዓት ምርጫ:-

በወር ከ**120** ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ ለሚሰሩ ተንከባካቢዎች በጣም የተሻለ። በወር 120 ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ እስኪሰሩ ድረስ የጥገኛዎ መድን ሽፋን አይጀምርም።

- ሙሉ የህክምና እና **$10** የጥርስ ህክምና (በወር $628-$697፣ እና ለመድን ሽፋንዎ $25 በወር)።
- ወይም የጥርስ ህክምና ሽፋን በወር **$10** ብቻ (በተጨማሪም በወር $25 ለመድን ሽፋንዎ)።

## አዲስ! $10 የጥርስ ህክምና መድን ሽፋን ለጥገኛዎች

120 ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ ከሰሩ

ስለ ጥገኛ ጥርስ በ **myseiu.be/oe-dep-dental** ላይ የበለጠ ይወቁ ወይም ኮዱን በስልክዎ ይቃኙት።

# ጥገኛን እንዴት መመዝገብና ማረጋገጥ እንደሚቻል

## ጥገኛ በኦንላይን ይመዝገቡ

1. የጤና ጥቅሞችን ማመልከቻ የጥገኛ ክፍል ይሙሉ እና Health: My Plan በመጠቀም ያስገቡ በ **myseiu.be/oe-myplan-22** እስከ ጁላይ 20።
2. በ 30 ቀናት ውስጥ የማረጋገጫ ደብዳቤ ያገኛሉ።

## ጥገኛን በመልዕክት ወይም በፋክስ ይመዝገቡ

1. የጤና ጥቅማጥቅሞች ማመልከቻ ላይ ያለውን የጥገኛ ክፍል ሞልተው እስከ ጁላይ 20 ድረስ በጤና ጥቅማጥቅሞች ማመልከቻ ላይ ወዳለው አድራሻ ይላኩ።
2. ማመልከቻዎን በጤና ጥቅማጥቅሞች ማመልከቻ ላይ ወዳለው አድራሻ በላኩ በ60 ቀናት ውስጥ ከጥገኛዎ(ችዎ) ጋር ያለዎትን ግንኙነት የሚያረጋግጥ ሰነድ ይላኩ።
3. በደመወዝ ቅነሳ መክፈል ይጀምሩ።

## ማስታወሻ፡- ማመልከቻዎ እንዲስተናገድ እስከ ጁላይ 20 ድረስ መግባት አለበት።

## በእኔ መድን ሽፋን ላይ ማንን መጨመር እችላለሁ?

ብቁ የሆኑ ልጆችን (እስከ 26ኛ የልደት በዓላቸው) በጥገኛ መድን ሽፋን መመዝገብ ይችላሉ። ጥገኞ(ዎችዎን) ለማስመዝገብ ከመረጡ፣ ከእነሱ ጋር ያለዎትን ግንኙነት ማረጋገጥ ያስፈልግዎታል። ብቁ ጥገኞችን ዝርዝር ለማግኘት **myseiu.be/oe-dv-22** ን ይጎብኙ።

## የጥገኝነት ማረጋገጫ

ጥገኛን መመዝገብ ከፈለጉ፣ ከእነሱ ጋር ያለዎትን ግንኙነት የሚያረጋግጥ ሰነድ መላክ ያስፈልግዎታል። የጥገኛዎን ማረጋገጫ እስኪልኩ ድረስ ማመልከቻዎ አልተጠናቀቀም። ማመልከቻዎን በሚያስገቡበት ተመሳሳይ ጊዜ ይህንን ማድረግ ይችላሉ (ከጤና ጋር በHealth: My Plan ወይም በፖስታ)፣ ነገር ግን ጥገኝነትዎን ለማረጋገጥ ማመልከቻዎ ከደረሰ 60 ቀናት በኋላ አለዎት።

## ለጥገኛ ማረጋገጫ ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች አይነቶች

ለጥገኛ ማረጋገጫ አንዳንድ ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች ከዚህ በታች አሉ። ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች ዝርዝር ለማግኘት **myseiu.be/oe-dep-ver** ን ይጎብኙ።

- የጥገኛዎ የልደት የምስክር ወረቀት ቅጂ።
- የጥገኛዎ አሳዳጊ፣ የህጋዊ ሞግዚትነት ወይም የጉዲፈቻ የምስክር ወረቀት ቅጂ።
- በጣም የቅርብ ጊዜ የፌደራል ግብር ተመላሽዎ ቅጂ።

## ጥገኛን ስለመመዝገብ የበለጠ ይወቁ


ሙሉ የጥገኞች ዝርዝር እና ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች በ **myseiu.be/oe-dep-ver** ያግኙ።

# ይመዝገቡ ወይም ለውጦችን ከHealth: My Plan ጋር ያድርጉ

## ለHealth: My Plan መለያ ይፍጠሩ

የሚከተሉትን መረጃዎች በመከተል እንደ አዲስ ተጠቃሚ ለመመዝገብ ወደ **myseiu.be/oe-myplan-22** ይሂዱ ወይም በስልክዎ ላይ ያለውን ካሜራ ይጠቀሙ:

እርምጃ **1:** እንደ አዲስ ተጠቃሚ ተመዝገብ የሚለውን ይምረጡ።




እርምጃ **2:** አባል መታወቂያ ወይም የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር (SSN) ይውሰዱ።





እርምጃ **3:** ዚፕ ኮድ እና የልደት ቀን ያስገቡ።





እርምጃ **4:** ውሎችን እና አስገዳጅ ሁኔታዎችን ገምግመው መስማማትዎን ያረጋግጡ።





እርምጃ **5:** የተጠቃሚ ስም፣ የይለፍ ቃል እና የደኅንነት ጥያቄውን ይሙሉ።




እርምጃ **6:** የእውቂያ መረጃ ይሙሉ እና መልእክት ልውውጥን ያስቀምጡ።




እርምጃ **7:** ማረጋገጫዎችን ያስቀምጡ።




ጥያቄዎች አሉዎት? ወደ **1-877-606-6705**፣ ከ 8 a.m. እስከ 6 p.m. ፓስፊክ ሰዓት አቆጣጠር፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ወደዚህ ይላኩ፦ **SEIU775BG-caregiver@magnacare.com**።

## ለመድን ሽፋን ይመዝገቡ

**እርምጃ 1:** በመለያ ይግቡ እና የእርስዎን የጤና መድን ሽፋን መረጃ ይመልከቱ ወይም ለመድን ሽፋን ይመዝገቡ።

ለመመዝገብ ብቁ ከሆኑ፣ በ ምዝገባ ጀምር የሚለው ላይ ጠቅ ለማድረግ የሚያስችል አማራጭ ያገኛሉ።




**እርምጃ 2:** በ**Health: My Plan** ላይ ያለውን የምዝገባ ሂደት ያሟሉ።

- የእርስዎን ዋና ሥራ ቀጣሪ ይምረጡ። ይህ ከእርስዎ ደመዎዝ ላይ በየወሩ የጣምራ ክፍያውን ድርሻ የሚቆርጠው አሠሪዎ ነው። የእርስዎ ዋና ሥራ ቀጣሪ እርስዎ በየወሩ በሠሩት የሥራ ሰዓታት ብዛት ላይ በመመርኮዝ ወደፊት ሌላ ሥራ ቀጣሪን ለእርስዎ ዳግመኛ ሊመድብ ይችል ይሆናል።
- ለእያንዳንዱ ጥቅም የብቁነት መረጃን ያያሉ።

**እርምጃ 3:** እንደሚከተሉት ያሉትን የእርስዎን ምርጫዎች አርትዕ ያድርጓቸው:-

- እንዴት እርስዎን ማግኘት እንደሚቻል - በኢሜይል፣ በስልክ ወይም በፖስታ ቤት።
- የእርስዎ ተመራጭ ቋንቋ።

**እርምጃ 4:** ለጤና መድን ሽፋን ይመዝገቡ:

- የሜዲካል መድን ዕቅድ - የእርስዎ መድን ዕቅድ እርስዎ እንደሚኖሩበት ቦታ የሚመረጥ ይሆናል።
- የጥርስ ሕክምና መድን ዕቅድ - የመድን ዕቅዶቹን ያነጻጽሯቸው እና ካሉት የጥርስ ሕክምና መድን ዕቅድ አማራጮች መካከል ይምረጡ።
- ጥገኛ ወደ መድን ሽፋንዎ ያክሉ እና ከእነሱ ጋር ያለዎትን ግንኙነት ያረጋግጡ። በገጽ 4 ላይ የበለጠ ይወቁ።
- እንደ ተንከባካቢ Kicks፣ EPIC Hearing እና Ginger ስላሉ ሌሎች የጤና ጥቅማ ጥቅሞች ይወቁ።

**እርምጃ 5:** የእርስዎን ምርጫዎች ይገምግሟቸው።

**እርምጃ 6:** ምዝገባውን ለማጠናቀቅ የእርስዎን መዳፊት (ማውስ) ወይም የንኪ ሰሌዳ (ተች-ስክሪን) በመጠቀም ስምዎትን ይፈርሙ።

የማረጋገጫ ማያ ገጽ (ስክሪን) ያያሉ እና ማረጋገጫ ኢሜይል እና ደብዳቤ ይላክልዎታል።

## በዕቅድዎ ላይ ይመልከቱ እና ለውጦችን ያድርጉ

**እርምጃ 1:** የእርስዎን የመድን ሽፋን ለማየት ወይም ለውጦችን ለማድረግ ወደ **Health: My Plan** ይግቡ።

**እርምጃ 2:** የሚከተሉትን ለማድረግ ከላይ በግራ ጥግ ያለውን የምናሌ /ሜኑ/ አዶውን ይጠቀሙ:-

- የእርስዎን የመድን ሽፋን አጭር ማጠቃለያ ማግኘት
- የእርስዎን ብቁነት እና የጥቅማ ጥቅም መረጃ መመልከት
- የእርስዎን የጥርስ ሕክምና የመድን ዕቅድ መለወጥ
- የእርስዎን የሥራ ሰዓታት ማየት።
- የራስ ክፍያዎችን መፈጸም እና ተጨማሪ ነገሮችን ማድረግ!

**በቀላሉ Health: My Plan ለመጠቀም በእርስዎ ስማርት ስልክ ላይ የ MyCreateHealth ሞባይል መተግበሪያን ያውርዱ።**

የ MyCreateHealth ሞባይል መተግበሪያ በእርስዎ iPhone ላይ በ App Store ወይም በእርስዎ Android ስልክ ላይ በ Google Play Store ላይ ይገኛል።




GET IT ON Google Play

Download on the App Store

# የጤና እንክብካቤ ዕቅድ ዋና፣ ዋና ነጥቦች

## በወር $25* ብቻ በመክፈል ከፍተኛ ጥራት ያለው የጤና እና የጥርስ ሕክምና የመድን ሽፋን ያግኙ

### የእርስዎ መድን ሽፋን የሚከተሉትን ጥቅማ ጥቅሞች ያካትታል:

- ነፃ ተቀዳሚ ዶክተር ጉብኝቶች
- ሜዲካል
- ኦርቶዶንቲያ
- የጥርስ ሕክምና
- የማየት ችሎታ
- መስማት ችሎታ
- መካንነት
- በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት
- የስሜት ድጋፍ

## ከእርስዎ መድን ሽፋን ማግኘት የሚችሉትን ሁሉ ጥቅም ያግኙ

### የሚፈልጉትን ዶክተር ያግኙ

በጣምራ ክፍያ ሊመረምርዎትና ሊያክምዎት የሚችል ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ዶክተር በመምረጥ ከሚያምኑት ዶክተር ጋር ጥሩ ግንኙነትን ያዳብሩ። ይህንን ዶክተር ለአጠቃላይ የጤንነት ማረጋገጫ ጉብኝቶች፣ ወይም ከታመሙ ወይም ወደ ስፔሺያሊስት ሪፈራል ካስፈለግዎት ሊያገኙት ይችላሉ።

በ Kaiser Permanente የድር ጣቢያ በኩል ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ዶክተርን መምረጥ ይችላሉ። ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ዶክተር መምረጥ ፈጣን እና ቀላል ነው። መለያ መፍጠር ላይ ወይም ዶክተር ማግኘት ላይ እገዛ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ:- **myseiu.be/oe-doctor**።

**የጤና እንክብካቤን በየትኛውም ቦታ** ከእርስዎ የመድን ሽፋን ጋር ምቹ፣ ነጻ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ከየትኛውም ቦታ ላይ ሆነው በአካል ተገኝቶ ከመታከም በተጨማሪ - በስልክ፣ በታብሌት፣ በኮምፒውተር አገልግሎት ያገኛሉ። ከፍተኛ ጥራት ያለው ግላዊነት የተላበሰ እንክብካቤ፣ ለደኅንነት አስተማማኝ እና ምቹ በሐኪም መታየቶችን እና የቴክኖሎጂ አማራጮችን በማግኘት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ። ለተጨማሪ **myseiu.be/ha-2022** ን ይመልከቱ።

### ማዳመጫ ጥቅሞች ያለ ጣምራ ክፍያ!

በEPIC ማዳመጫ በኩል፣ ምንም የጣምራ ክፍያ ሳይኖር ለእያንዳንዱ ጆሮ $1,200 ዋጋ ያለው የማዳመጫ ሃርድዌር ማግኘት ይችላሉ። የበለጠ በ **myseiu.be/hearing** ላይ ይረዱ።

## ለእርስዎ ብቻ ይበልጥ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ጥቅማ ጥቅሞች

### ለራስ እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ ነው:- የስሜታዊ ጤና ጥቅማ ጥቅሞች

የስሜታዊ ጤና ልክ እንደ አካላዊ ጤናዎ ሁሉ አስፈላጊ ነው። የመድን ሽፋኑ ሳይኮቴራፒ፣ መድኃኒት፣ በቡድን የሚሰጥ ቴራፒ እና ተጨማሪ እና አማራጭ መድኃኒቶችንም ጭምር ያካትታል:-

- በነጻ እና ለደኅንነት አስተማማኝ በሆነ የጽሑፍ መልእክት መላላክ በኩል ለእርስዎ ምክር እና እገዛ መስጠት ከሚችል ኤክስፐርት አሠልጣኝ ጋር የ Ginger መተግበሪያ ቀላል ያደርግልዎታል። እዚህ ላይ የበለጠ ይረዱ:- **myseiu.be/oe-ginger**።
- ወደ Behavioral Health Access Line በ Kaiser ላይ በስልክ ቁጥር **1-888-287-2680** ይደውሉ ወይም ይጎብኙ **myseiu.be/kaiser-bh**።
- **በዚህ ዓመት አዲስ!** ከቴራፒስት ጋር ለመነጋገር የአእምሮ ጤና እክብካቤ ውይይትን ይጠቀሙ። የበለጠ ለማወቅ **www.kp.org/wa** ን ይጎብኙ።




በየዓመቱ የእርስዎን Caregiver Kicks — ማዳለጥን የሚከለካል ጫማ — በእያንዳንዱ አመት፣ ብቁ እስከሆኑ ድረስ ያግኙ! ይህ ምቹ ጫማ ሲሆን በሥራ ቦታ ላይ ደኅንነትዎን ይጠብቅልዎታል ብሎም ያምራል። እንደ Reebok እና Skechers ከመሳሰሉ ታዋቂ ስም ያላቸው ምርቶች የመጡ ከ70 በላይ በሆኑ ስታይሎች ይገኛል። የእርስዎን Caregiver Kicks እዚህ ላይ ያግኙ:- **myseiu.be/oe-kicks**።

### ብቁ መሆንዎን እርግጠኛ አይደሉም?

ብቁ መሆንዎን ለማረጋገጥ **myseiu.be/oe-myplan-22** ን ይጎብኙ።

*የግል መድን ሽፋን ዋጋ በወር $25 ነው (የጣምራ ፕሪሚየም ተብሎም ይጠራል)። ጥገኞችን ለመመዝገብ ከመረጡ፣ የእርስዎ ወርሃዊ ወጪ ከፍ ያለ ይሆናል። ስለ ዋጋ ዝርዝሮች ገጽ 4ን ይመልከቱ። **ከተቀዳሚ ተንከባካቢ ዶክተርዎ ጋር የሚደረጉ ጉብኝቶች የጣምራ ክፍያ የላቸውም፣ ነገር ግን ዶክተርዎ ምርመራዎችን ወይም የላብራቶሪ ሥራዎችን ካዘዘ፣ ለእነዚያ አገልግሎቶች የጣምራ ክፍያ መክፈል ሊኖርብዎ ይችላል።




## የእርስዎን በሐኪም የተሰጠ መድኃኒት ማዘዣ በብልህነት ይጠቀሙበት

ሁሉንም ያልዎትን ምርጫዎች እና ምን ያክል ወጪ እንደሚጠይቁ በመረዳት በእርስዎ በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት የመድን ሽፋን ማግኘት የሚችሉትን ጥቅም በሙሉ ያግኙ።

*ሥራ የሚሠሩት ለሃይማኖታዊ ተቋም ከሆነ፣ የእርስዎ የጤና መድን በሃይማኖት ምክንያት ያለመከታተትን በሚፈቀደው በ Affordable Care Act ሕግ መሠረት የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን መድን ሽፋን አያካትትም። ሆኖም ግን፣ በጤና መድን ሽፋን ውስጥ የተመዘገቡ እስከሆኑ ድረስ ከ Sav-Rx እነዚህን አገልግሎቶች እርስዎ ምንም ወጪ ማውጣት ሳይኖርብዎት (እና ሌላ ምንም ተጨማሪ እርምጃ መውሰድ ሳያስፈልግዎት) የሚያገኙ ይሆናል።

**እነዚህ ዋጋ ላይ የተመረኮዙ መድኃኒቶች የተለያዩ የጤና ችግሮችን ለማከም የተዘጋጁ ጀነሪክ መድኃኒቶች ናቸው።

| Rx ጥምራ ክፍያ (በአውታረ መረብ ውስጥ) ለ 30 ቀናት ለሚሆን መድኃኒት አቅርቦት | በመድኃኒት ቤት ውስጥ | በፖስታ ቤት ትዕዛዝ |
|---|---|---|
| ጀነሪክ የወሊድ መከላከያ መድኃኒቶች* | $0 | $0 |
| ዋጋ ላይ የተመረኮዙ መድኃኒቶች** | $4 | $0 በ 30 ቀን አቅርቦት |
| ጀነሪክ መድኃኒቶች | $8 | $3 በ 30 ቀን አቅርቦት |
| ፎርሙላሪ ታዋቂ ስም ያላቸው መድኃኒቶች | $25 | $20 በ 30 ቀን አቅርቦት |

## ድንገተኛ የሕክምና ክፍልን ከመጠቀም ውጭ ያሉ አማራጮች

| የድንገተኛ ሕክምና ክፍል $200 ጣምራ ክፍያ | አስቸኳይ ሕክምና $0 ጣምራ ክፍያ | ተቀዳሚ ዶክተር / ኦንላይን ጉብኝቶች ነጻ |
|---|---|---|

አስቸኳይ የሕክምና እንክብካቤን በመጠቀም **$200** ገንዘብ ይቆጥቡ።
አፋጣኝ የሕክምና እርዳታ ማግኘት የሚያስፈልግዎት ከሆነ፣ በአቅራቢያዎ የሚገኝ የአስቸኳይ ሕክምና መስጫ ማዕከልን ያፈላልጉ ወይም ከእርስዎ ዶክተር ጋር በተመሳሳይ ቀን ቀጠሮ ይያዙ። እስከ $200 ድረስ ገንዘብ መቆጠብ ይችላሉ።

አፋጣኝ ሕክምና እንክብካቤ እንደ ድንገተኛ ሕክምና አይደለም።
እንደ ልብ ድካም ወይም ስትሮክ በመሰለ ለሞት አደጋ ሊያጋልጥ በሚችል የጤና ችግር ውስጥ ካሉ፣ ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ አለብዎት። እንደ የቁርጭምጭሚት ወለምታ የመሰለ ቀላል የሆኑ የአካል ጉዳት ወይም መቁሰል ካለብዎት ወደ አስቸኳይ ሕክምና ክፍል ይሂዱ።

# የሜዲካል መድን ሽፋን ጥቅማጥቅም አጭር ማጠቃለያ

HMO ዕቅድ አጭር ማጠቃለያ
ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን፡- 08/01/2022

ይህ የመድን ጥቅማጥቅሞች አጭር ማጠቃለያ ነው። ይህ ውል ወይም የመድን ሽፋን ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አይደለም። አማራጭ ሕክምናዎችን ጨምሮ ሁሉም የጥቅማ ጥቅም ማብራሪያዎች በሕክምና አስፈላጊ ለሆኑ አገልግሎቶች የሚሰጡ ናቸው። አባሉ የመድን ሽፋን ላለው አገልግሎት ወይም ለአገልግሎቱ በተጨባጭ የሚከፈለውን ክፍያ ያነሰ የድርሻ ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል። ገደቦችን ጨምሮ ሙሉ የመድን ሽፋን ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት፣ እባክዎ የእርስዎን የመድን ሽፋን ምስክር ወረቀት ይመልከቱ። በ Patient Protection and Affordable Care Act of 2010 ሕግ መሠረት፡-

- የኤጀንሲው አገልግሎት አቅራቢዎች እና CDWA የግለሰብ አቅራቢዎች ብቻ፡- ጥገኞች እስከ 26ኛው የልደት በዓላቸው ድረስ በዚህ እቅድ ውስጥ ለመመዝገብ ብቁ ናቸው። ለእርስዎ ጥገኞች ሙሉን የአርቦን (ፕሪሚየም) ክፍያ የመክፈል ኃላፊነቱን እርስዎ ይወስዳሉ። ስለ አርቦን ተመኖች ለማወቅ የእርስዎን ቀጣሪ ድርጅት ወይም ግለሰብ ያነጋግሩ።

| ጥቅማ ጥቅሞች | በአውታረ መረብ ውስጥ |
|---|---|
| ተቀናሽ ገንዘብ ከዕቅዱ | ዓመታዊ ያልሆነ ተቀናሽ |
| ነፍስ ወከፍ ተቀናሽ ወደ ሌላ የሚተላለፍ | ተገቢነት የለውም |
| ጥምር ኢንሹራንስ ዕቅድ | ጥምር ኢንሹራንስ ዕቅድ የለም |
| ከኪስ የሚከፈል ገንዘብ ገደብ | ግለሰብ ከኪሱ አውጥቶ የሚከፈለው ገንዘብ ገደብ፡- $1,200<br>ቤተሰብ ከኪሱ አውጥቶ የሚከፍለው ገንዘብ ገደብ $2,400<br>ለሚከተሉት የመድን ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶች ከኪስ የሚከፈል ገንዘብ በከኪስ የሚከፈል ገንዘብ ገደብ ውስጥ የተካተቱ ናቸው፡-<br>የመድን ሽፋን ላላቸው ሁሉም የወጪ መጋራቶች |
| ቅድመ የነበረ ጤና ችግር (PEC) መጠበቂያ ጊዜ | ምንም PEC የሌለው |
| የዕድሜ ልክ ከፍተኛው | ገደብ የሌለው |
| የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች (የሐኪም ምርመራዎች) | ጣምራ ያልሆኑ ተቀዳሚ ክፍያዎች የሉም/$15 ጣምራ ክፍያ ስፔሻሊቲ |
| የሆስፒታል አገልግሎቶች | ለተኙት ታካሚ የሚሰጡ አገልግሎቶች፡- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት።<br>አስቀድሞ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል ወይም የመድን ሽፋን አይኖረውም።<br>የተመላላሽ ታካሚ ቀዶ ጥገና፡- $50 ጣምራ ክፍያ |
| በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች (አንዳንድ በመርፌ የሚሰጡ መድኃኒቶች በተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች ሥር የመድን ሽፋን ሊኖራቸው ይችላል) | በዋጋ ላይ የተመረኮዘ/ተመራጭ ጄነሪክ መድኃኒት (ታየር 1)/ተመራጭ ታዋቂ ስም ያለው ምርት (ታየር 2)<br>$4/ $8/ $25 ጣምራ ክፍያ በ 30 ቀን አቅርቦት |
| በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት በፖስታ ቤት የሚሰጥ ትዕዛዝ | $5 ዋጋ ቅናሽ በ 30 ቀን አቅርቦት |
| የደረቅ መርፌ ሕክምና (አኩፓንክቸር) | በአንድ የቀን መቁጠሪያ ዓመት ውስጥ እስከ 8 ለሚደርሱ ጉብኝቶች በሕክምና ምርመራው መሠረት የመድን ሽፋን ይኖረዋል፣ ተጨማሪ ጉብኝቶች ፈቃድ በመድን ዕቅዱ ፈቃስ ሲያገኙ - ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል |

| ጥቅማ ጥቅሞች | በአውታረ መረብ ውስጥ |
|---|---|
| የአምቡላንስ አገልግሎቶች | የመድን ሽፋኑ 80% ይከፍላል እርስዎ 20% ይከፍላሉ |
| የኬሚካል ጥገኝነት | ተኝቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት፣ አስቀድሞ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል ወይም የመድን ሽፋን አይኖረውም።<br>ተመላላሽ ታካሚ:- $0 ጣምራ ክፍያ |
| መሣሪያዎች፣ ማሽኖች እና አቅርቦቶች | በ50% መድን ሽፋን ያላቸው።. አስቀድሞ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል ወይም የመድን ሽፋን አይኖረውም።<br>• ረዥም ጊዜ የሚቆይ ሜዲካል መሣሪያ<br>• ኦርቶፔዲክ (የአጥንት) ኦጋዥ ሕክምና መገልገያዎች<br>• ድኅረ ማስቴክቶሚ ብራዎች (የሕክምና ጡት ማስያዣዎች) እስከ ሁለት (2) በየስድስት (6) ወሩ የተገደበ<br>• የኦስቶሚ አቅርቦቶች<br>• ፕሮስቴቲክ መሣሪያዎች |
| የስኳር በሽታ አቅርቦቶች | ኢንሱሊን፣ መርፌዎች፣ ሲሪንጆች እና ላንሴትሲ በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች። ከውጭ የሚሰጥ ኢንሱሊን መግፊያ (ፓምፖች)፣ የደም ግሉኮስ መቆጣጠሪያዎች፣ የምርመራ ሪኤጀንቶች እና አቅርቦቶች — መሣሪያዎች፣ ማሽኖች እና አቅርቦቶች የሚለውን ይመልከቱ። መሣሪያዎች፣ ማሽኖች እና አቅርቦቶች ወይም በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች የመድን ሽፋን ሲኖራቸው እና የመድን ሽፋን ገደቦች ሲኖርባቸው የስኳር በሽታ አቅርቦቶች እነዚህ ገደቦች አይመለከታቸውም። |
| የምርመራ ላብራቶሪ ኣና የራጂ አገልግሎቶች | ተኝቶ ታካሚ:- በሆስፒታል አገልግሎቶች ሥር የመድን ሽፋን ያለው<br>ተመላላሽ ታካሚ:- ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው፣ MRI/PET/CT $50 ጣምራ ክፍያ<br>ከፍተኛ የራዲዮሎጂ ኢሜጂንግ አገልግሎቶች እንደ CT፣ MR እና PET የመሳሰሉ በሕክምና አስፈላጊ እንደሆኑ መረጋገጥ አለባቸው እንዲሁም ከድንገተኛ ሕክምና ወይም የተኝቶ ታካሚ አገልግሎቶች ጋር የተገናኙ ካልሆነ በቀር በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘትን ይጠይቃሉ። |
| የድንገተኛ አደጋ አገልግሎቶች<br>(ተኝቶ እንዲተኩም ከተደረገ ጣምራ ክፍያ በይለፈኝ ይታሰፋል) | $200 ጣምራ ክፍያ በተመደበ ተቋም<br>$200 ጣምራ ክፍያ ባልተመደበ ተቋም |
| የጆሮ ምርመራዎች (መደበኛ) | $0 ጣምራ ክፍያ |
| ኦጋዥ ማዳመጫ መሣሪያ | በተለየ የመድን ዕቅድ የሚሸፈን:- EPIC ማዳመጫ። ጣምራ ክፍያ የለም፣ እስከ $1,200 በየእያንዳንዱ ጆሮ በየ 3 ዓመታት ኦጋዥ ማዳመጫውን ወጪ ለመሸፈን። የበለጠ በ myseiu.be/hearing ላይ ይረዱ |
| የቤት ውስጥ የጤና አገልግሎቶች | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው። ምንም የምርመራ ገደቦች የሉም። አስቀድሞ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል ወይም የመድን ሽፋን አይኖረውም። |
| የሆስፒስ አገልግሎቶች | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው። አስቀድሞ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል ወይም የመድን ሽፋን አይኖረውም። |
| የመካንነት ሕክምና አገልግሎቶች | አርቴፊሻል የወንድ ዘር ማመንጨት፣ ኢን-ቪትሮ እንቁላል ማቋት እና የመድኃኒት ሕክምና ጨምሮ ለወንድ እና ለሴት መካንነት ሕክምና የሚሰጡ ሜዲካል እና የቀዶ ጥገና አገልግሎቶች እና ሁሉም ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶች ተገቢነት ያላቸው የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች የወጪ መጋራቶች እንደተጠበቁ ሆነው እስከ $5,000 በዕድሜ ልክ ከፍተኛ ድረስ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል።<br><br>የመካንነት መድኃኒቶች ተቀናሾች እና 20% የመድን ሽፋን ጣምራ ኢንሹራንስ ዕቅድ መሠረት የመድን ሽፋን አላቸው፣ እስከ $5,000 በዕድሜ ልክ ከፍተኛ ድረስ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል። |
| ማኑፒሌቲቭ ቴራፒ | ያለ ምንም ቅድሚያ ፈቃድ በአንድ የቀን መቁጠሪያ ዓመት እስከ 10 ምርመራዎች - $0 ጣምራ ክፍያ። |
| የማሳጅ አገልግሎቶች | የመልሶ መቋቋሚያ አገልግሎቶችን ይመልከቱ |

| ጥቅማ ጥቅሞች | በአውታረ መረብ ውስጥ |
|---|---|
| የእመጫትነት አገልግሎቶች | ተኝቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት<br>ተመላላሽ ታካሚ:- $0 ጣምራ ክፍያ። መደበኛ ሕክምና የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች ጣምራ ክፍያ አይመለከተውም። |
| የአእምሮ ጤና | ተኝቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት። አስቀድሞ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል ወይም የመድን ሽፋን አይኖረውም።<br>ተመላላሽ ታካሚ:- $0 ጣምራ ክፍያ |
| ናቹሮፓዚ | በአንድ የቀን መቁጠሪያ ዓመት ውስጥ እስከ 3 ለሚደርሱ ጉብኝቶች በሕክምና ምርመራው መሠረት የመድን ሽፋን ይኖረዋል፣ ተጨማሪ ጉብኝቶች ፈቃድ በመድን ዕቅዱ ፈቃስ ሲያገኙ - ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል $0 ጣምራ ክፍያ |
| የአራስ ሕፃን አገልግሎቶች | የመጀመሪያ የሆስፒታል ቆይታ:- የሆስፒታል አገልግሎቶችን ይመልከቱ፣ የሐኪም ምርምራዎች:- የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶችን ይመልከቱ፤ መደበኛ የጤና ምርመራ አገልግሎት:-<br>መከላከያ እንክብካቤን ይመልከቱ።<br>ለአራስ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚነት ያለው ማናቸውም የወጪ መጋራት ከእናትየው የተለየ ነው> |
| ከቅጥ ያጣ ውፍረት ጋር የተገናኙ አገልግሎቶች | የሕክምና መስፈርት ሲሟላ በወጪ መጋራት ወቅት ሽፋን ይኖረዋል |
| የውስጥ ብልት ትክለ ነቀላዎች | ገደብ የሌለው፣ ምንም መጠበቂያ ጊዜ የለውም<br>ተኝቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት<br>ተመላላሽ ታካሚ:- $0 ጣምራ ክፍያ |
| የመከለከያ እንክብካቤ:-<br>የጤናማነት እንክብካቤ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ክትባት፣ ፓፕ ስሚር ምርመራዎች፣ ማሞግራሞች | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው<br>የሴቶች መከለከያ እንብካቤ አገልግሎቶች (የወሊድ መከላከያ ዘዴ መድኃኒቶች ኣና መሣሪያዎች እንዲሁም መሃን ማድረግ ጨምሮ)<br>ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን አላቸው። |
| የመልሶ መቋቋሚያ አገልግሎቶች:-<br>የመልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች በቀን መቁጠሪያ አንድ ዓመት ውስጥ ያሉት ምርመራዎች ድምር ጥምረት ነው | ተኝቶ ታካሚ:- 60 ቀናት በቀን መቍጠሪያ አንድ ዓመት። ከአእምሮ ጤና ምርመራ ጋር የተገናኙ አገልግሎቶች ያለ ምንም ገደብ የመድን ሽፋን አላቸው።<br>$100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት። አስቀድሞ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል ወይም የመድን ሽፋን አይኖረውም።<br>ተመላላሽ ታካሚ:- 60 ምርመራዎች በቀን መቍጠሪያ አንድ ዓመት። ከአእምሮ ጤና ምርመራ ጋር የተገናኙ አገልግሎቶች ያለ ምንም ገደብ የመድን ሽፋን አላቸው።<br>ጣምራ ያልሆኑ ተቀዳሚ ክፍያዎች የሉም/$15 ጣምራ ክፍያ ስፔሻሊቲ |
| የሠለጠነ የነርስ አገልግሎት ተቋም | በአንድ የቀን መቁጠሪያ ዓመት እስከ 60 ቀናት የመድን ሽፋን ያለው። |
| መሀን ማድረግ<br>(ቫስከቶሚ፣ ቲዩባል ሊጌሽን) | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው። |
| Temporomandibular Joint (TMJ)<br>አገልግሎቶች | ተኝቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት<br>ተመላላሽ ታካሚ:- $0 ጣምራ ክፍያ |
| የሲጋራ ማቆም ምክር አገልግሎት | ከዕድሜ ልክ ፕሮግራም አቋርጦ መውጣት - ሙሉ በሙሉ መድን ሽፋን ያለው |
| መደበኛ የምርመራ አገልግሎት<br>(1 ምርመራ በየ 12 ወሩ) | $0 ጣምራ ክፍያ |
| ኦፕቲካል (የዓይን) መገልገያዎች።<br>ሌንሶችን እና ኮንታክት ሌንሶችን<br>እና ፍሬሞችን ጨምሮ | ዕድሜያቸው ከ**19** በታች የሆኑ አንድ የመንጽር ፍሬም እና መስታውት በዓመት ወይም በ50% ጣምራ ኢንሹራንስ መድን ሽፋን ያላቸው ኮንታክት ሌንሶች<br>የአባል ዕድሜ **19** እና ከዚያ በላይ $300 በየ 12 ወራት |

# የእርስዎ የጥርስ ሕክምና የመድን ዕቅዶች ምርጫ

| አገልግሎት ሰጪዎች | ዓመታዊ ከፍተኛ | ተቀናሽ | ለተለመዱ ምርመራዎ የጣምራ ክፍያ | ልዩ ባሕሪያት |
|---|---|---|---|---|
| DELTA DENTAL | $2,000 | $0 | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው | • ገጠራማ አካባቢዎችን ጨምሮ መጠነ ሰፊ የአገልግሎት ሰጪዎች አውታረ መረብ። <br> • የPacific Dental Alliance (PDA) የጥርስ ሐኪም ሲጎበኙ ነፃ የ Sonicare የጥርስ ብሩሽ ያግኙ። እዚህ ላይ የበለጠ ይረዱ፦ **myseiu.be/oe-pda**። <br> • ከፍተኛው እስከ $2,000 የሚደርስ የነፃ የጥርስ ህክምና ከ PDA የጥርስ ሀኪም ያግኙ! |
| Willamette Dental Group | ምንም | $0 | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው | • በ 1-5 ኮሪደር ውስጥ የሚኖሩ ምቹ የሆኑ እንክብካቤ ሰጪዎች። <br> • ከፍተኛ የጥርስ ሕክምና ወጪዎች ላሉባቸው እንክብካቤ ሰጪዎች ምንም ዓመታዊ ከፍተኛ አይኖርም። <br> • የ Willamette የጥርስ ህክምና አቅራቢን ማየት አለብዎት። |

## የእርስዎ የጥርስ ሕክምና የመድን ዕቅድ በእርስዎ ወርኃዊው ጣምራ አርቦን (ፕሪሚየም) **$25** ላይ የተጠቃለለ ነው።

- ሁለቱም የጥርስ ሕክምና መድን ኦቅዶች የኦርቶዶንቲያ ጥቅማ ጥቅሞችን ያቀርባሉ።
- የጥርስ ህክምና ዕቅድዎን ለመቀየር የጤና ጥቅማጥቅሞች ማመልከቻን ሞልተው ይመልሱ። የእርስዎ ማመልከቻ እንዲሰራ እስከ ጁላይ 20 ድረስ መግባት አለበት።
- **በዚህ ዓመት አዲስ!** የ120 ሰዓት ምርጫን የመረጡ APዎች እና CDWA IPዎች ጥገኞቻቸውን በጥርስ ህክምና መድን ሽፋን በወር $10 ብቻ። እዚህ ላይ የበለጠ ይረዱ፦ **myseiu.be/oe-dep-dental** የጥርስ ሕክምና።

DELTA DENTAL®

# ፒፒኦ ዕቅድ

**ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን 8/1/2022**

ጥቅማ ጥቅም የሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ፡- 1/1/2023 - 31/12/2023
የጥቅማ ጥቅም የሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ* (በግለሰብ፤ በክላስ 1 ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም)፡- $2,000
ኦርቶዶንቲያ - ዓዋቂ ሰዎች እና ሕፃናት፡- 50%
የዕድሜ ልክ ከፍተኛው (በግለሰብ)፡- $2,000

| | Delta Dental PPO Dentist | Delta Dental Premier Dentist | ተሳታፊ ያልሆነ የጥርስ ሐኪም |
|---|---|---|---|
| **ጥቅማ ጥቅም የሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ ተቀናሽ** | | | |
| በአውታረ መረብ ውስጥ ላለ ክላስ 1 ተፈጻሚ አይሆንም - በአውታረ መረብ ውስጥ ተቀናሽ የለም - $50 በእያንዳንዱ የጥቅማ ጥቅም የሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ | $0/$50 | $50 | $50 |
| **ክላስ 1 - የሕክምና ምርመራ እና መከላከያዎች** | | | |
| ምርመራዎች<br>ጽዳት ሥራ<br>ፍሎራይድ<br>ራጂዎች<br>ሲላንቶች | 100% | 80% | 80% |
| **ክላስ 2 - ጥገና ሥራ** | | | |
| ማገገሚያዎች<br>ፖስቲሪየር ኮምፖዚት ሙሌቶች<br>ኢንዶዶንቲክስ (ሩት ካናል)<br>ፔሪዮዶንቲክስ<br>የአፍ ቀዶ ጥገና ሕክምና | 100% | 60% | 60% |
| **ክላስ 3 - ከፍተኛ ሕክምና** | | | |
| ዴንቸሮች<br>ከፊል ዴቸሮች<br>ኢምፕላንትስ<br>ብሪጆች<br>ክራውንስ | 80% | 40% | 40% |

እባክዎ ልብ ይበሉ፡- ይህ ለንጽጽር ዓላማዎች ብቻ የቀረቡ የጥቅማ ጥቅሞች አጭር ማጠቃለያ ነው እና እንደ አገልግሎት ውል ሆኖ ሊቆጠር አይችልም። በአንድ የመድን ዕቅድ ውስጥ አንድ ጊዜ ከተመዘገቡ በኋላ፣ የእርስዎን Delta Dental PPO መድን ዕቅድ ይበልጥ ዝርዝሮችን የሚሰጠውን የእርስዎን የጥቅማ ጥቅሞች አነስተኛ መጽሐፍ ማግኘት ይችላሉ። ማናቸውም ጥያቄ ካልዎት ወደ የእኛ የደንበኛ አገልግሎት ክፍል ለመደወል እባክዎ ነጻ ይሁኑ ወይም የእኛን የድር ጣቢያ DeltaDentalWA.com ይጎብኙ።

# ከእርስዎ ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘት የሚችሉትን ሁሉ ያግኙ!

### የMySmile® መለያ ይፍጠሩ

ወደ የእርስዎ መታወቂያ ካርድ፣ የጥቅማ ጥቅሞች መረጃ፣ ከኪስ ወጪ ተደርጎ የሚከፈል ገንዘብ ግምቶች እና ተጨማሪ ነገሮችን ለደኅንነት አስተማማኝ የሆነ፣ በቀን 24 ሰዓት/በሳምንት 7 ቀን መዳረሻ ያግኙ! የእኛ "Find your member ID" መሣሪያ ምዝገባ ማከናወንን ቀላል ያደርገዋል። የእርስዎን መለያ ለመፍጠር DeltaDentalWA.com ን ይጎብኙ።

### በአውታረ መረብ ውስጥ የጥርስ ሀኪም ይምረጡ

የእርስዎ የመድን ዕቅድ ወደ Delta Dental PPO አውታረ መረብ መዳረሻ ይሰጡዎታል። ሆኖም ግን፣ የሚገኙት ጥቅማ ጥቅሞች Delta Dental PO የጥርስ ሐኪምን በሚጎበኙበት ጊዜ ከዚህም በላይ ብዙ ርቀት ይሄዳሉ። በእርስዎ አውታረ መረብ ውስጥ ያለ የጥርስ ሐኪምን ለማግኘት DeltaDentalWA.com ን ይጎብኙ (እንዴት እንደሚቻል በሚቀጥለው ገጽ ላይ ይረዱ)።

የእርስዎ የመድን ዕቅድ አስፈላጊ ከሆነ ከእርስዎ አካባቢ ውች ያለ የ PPO ጥርስ ሐኪምን ማግኘት እንዲችሉ መዳረሻ ከሚሰጥዎት Delta Dental Premier® አውታረ መረብ ጋር አብሮ ይመጣል። ይህ ማለት ከአውታረ መረብ ውጭ ያሉ ከፍተኛ ወጪዎችን ከመክፈል ይቆጠባሉ ማለት ነው (ከዚህ በታች ያለውን ቻርት ይመልከቱ)።

### ተጨማሪ የጥርስ ህክምና ስራ ተሸፍኗል

የክላስ I ወጪዎች በእርስዎ ዓመታዊ ከፍተኛ ላይ አይቆጠሩም፣ ይህም ማለት አብዛኛው የእርስዎ የክላስ II እና III ወጪዎች በመድን ኢንሹራንሱ የሚሸፈኑ ይሆናሉ ማለት ነው።

| | PPO | ፕሪሚየር | ከአውታረ መረብ ውጭ |
|---|---|---|---|
| የእርስዎ የመድን ዕቅድ የጥርስ ሕክምና አውታረ መረብ | ✓ | | |
| ጥቅማ ጥቅሞች ብዙ ርቀት ይሄዳሉ ይህም ማለት ከኪስ ወጪ የሚከፈለው ገንዘብ አነስተኛ ይሆናል | ✓ | | |
| የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅጾች ፋይሎች ለእርስዎ | ✓ | ✓ | |
| ከእኛ የጥራት አስተዳደር እና የወጪ ጥበቃ ጋር አብሮ ይመጣል | ✓ | ✓ | |
| ምንም የወጪ ጥበቃ የለም ማለት ከኪስ ወጪ የሚከፈለው ገንዘብ ከፍተኛ ይሆናል | | | ✓ |

### በእርስዎ አቅራቢያ በአውታረ መረብ ውስጥ ያለ የጥርስ ሐኪምን ያግኙ

1. ይህን ይጎብኙ **DeltaDentalWA.com**
2. በ 'ኦንላይ መገልገያዎች (Online Tools)' ላይ ጠቅ ያድርጉ እና የእኛን 'የጥርስ ሃኪም አግኝ (Find a Dentist)' መሣሪያ ይጠቀሙ
3. የእርስዎን የፍለጋ ውጤቶች ለማጣራት 'Delta Dental PPO' ይምረጡ

### በእርስዎ የጥርስ ሐኪም በመደበኛነት ይታዩ።

የእርስዎ መድን ዕቅድ በየዓመቱ የሚደረጉ የመከላከያ እንክብካቤዎችን ይሸፍናል። በየቀኑ ጥርስን ማጽዳት እና በመደበኛነት በሐኪም መታየት የእርስዎን ፈገግታ ጤናማ ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ እና ስቃይ የተሞላ ውድ ችግሮችን ከመምጣታቸው በፊት ለመከላከል አስፈላጊ ናቸው።

### ከኪስ ወጪ ሆኖ የሚከፈል ክፍያ መጠን ግምቶች።

የእርስዎን ወጪ ማወቅ መቻል እርስዎን እና የእርስዎን የጥርስ ሐኪም የእርስዎን ጥቅማ ጥቅሞች ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ ሕክምናውን ዕቅድ እንዲታወጡለት ያግዛችኋል።

**MySmile Cost Genie℠** ቅጽበታዊ የወጪ መጠን ግምቶችን ይሰጥዎታል። እንደ ሙሌቶች ለመሳሰሉ መሠረታዊ ሕክምናዎች በጣም ጥሩ ነው። ለእርስዎ በግል የተዘጋጁ ግምቶችን ለማግኘት ወደ የእርስዎ MySmile መለያ በቀላሉ ይግቡ።

እንደ ክራውን የመሳሰለ የተራዘመ ሕክምና በሚፈልጉበት ጊዜ የእርስዎን የጥርስ ሐኪም "ቅድሚያ ግምት ማረጋገጫ" እንዲሰጥዎት ይጠይቁ። ከእርስዎ የጥርስ ሐኪም የሕክምና እና ወጪ ማረጋገጫ ያገኛሉ። ይህ የእርስዎን የሕክምና ዕቅድ፣ የእርስዎ የመድን ዕቅድ ምንን እንደሚሸፍን እና ለእርስዎ የጥርስ ሐኪም ምን ያክል መክፈል እንዳለብዎት ዝርዝር ይሰጣል።

## ጥያቄዎች አሉዎት?
## ወደ **Delta Dental** ይደውሉ።
## **1-800-554-1907**

ከሰኞ እስከ ዓርብ:- 7 a.m. እስከ 5 p.m.
በፓስፊክ ሰዓት አቆጣጠር

እንደ አዲስ ታካሚ የPacific Dental Alliance (PDA) አቅራቢን ለሚጎበኙ የDelta Dental አባላት:- ነፃ የሶኒኬር የጥርስ ብሩሽ ሊያገኙ ይችላሉ።

ለተሟላ PDA አቅራቢ ዝርዝር **myseiu.be/oe-pda** ን ይጎብኙ።

Willamette
Dental Group

# የጥርስ ሕክምና ዕቅድ

ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን **8/1/2022**

ጥያቄዎች አሉዎት?
እዚህ ላይ የበለጠ ይረዱ:-
**myseiu.be/oe-willamette**።

በ Willamette Dental of Washington, Inc የተጻፈ። ይህ የመድን ዕቅድ የጥርስን እና ደጋፊ ሥጋዎችን በሽታዎች ወይም የጤና ችግሮች ለመከላከል፣ ለመመርመር ወይም ለማከም የሚያስችሉ የተራቀቁ የአገልግሎቶችን ሽፋን ያቀርባል። እዚህ ላይ የቀረቡት አብዛኛዎቹ በብዛት በእርስዎ የመድን ሽፋን ዕቅድ ላይ ካሉ አሠራሮች መካከል አንዳንዶች ናቸው። ሙሉ የመድን ሽፋን ዕቅድ ዝርዝር ማብራሪያን፣ ገደቦችን እና ተለይተው የሚቀሩ ነገሮችን ለማግኘት የመድን ሽፋን ምስክር ወረቀቱን እባክዎ ይመልከቱ።

| ጥቅማ ጥቅሞች | ጣምራ ክፍያዎች |
|---|---|
| ዓመታዊ ከፍተኛ | ምንም ዓመታዊ ከፍተኛ የለም* |
| ተቀናሽ | ምንም ተቀናሽ የለም |
| አጠቃላይ እና የኦርቶዶንቲክ የሐኪም ምርመራዎች | ምንም የጣምራ ክፍያ በእያንዳንዱ ምርመራ አይኖርም |
| **ምርመራ እና መከላከያ አገልግሎቶች** | |
| መደበኛ እና ድንገተኛ ምርመራዎች፣ ራጂዎች፣ የጥርስ ማጽዳት፣ የፍሎራይድ ሕክምና፣ ሲያላንቶች (በእያንዳንዱ ጥርስ)፣ የጭንቅላት እና የአንገት ካንሰር ምርመራ፣ የአፍ ንጽሕና መመሪያ፣ ፔሪዶንታል ቻርቲንግ፣ ፔሪዶንታል ምርመራ | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| **የጥገና የጥርስ ሕክምና ሥራ** | |
| ሙሌቶች (አማልጋም) | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| ፕሮክሌን-ሜታል ክራውን | እርስዎ $250 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **ፕሮስቶንዶንቲክስ** | |
| የላይኛው ወይም የታችኛው ሙሉ ዴንቸር | እርስዎ $400 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| ብሪጅ (በጥርስ) | እርስዎ $250 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **ኤንዶቶንቲክስ እና ፔሪዮዶንቲክስ** | |
| የሩት ካናል ቴራፒ - አንተሪዮር | እርስዎ $85 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| የሩት ካናል ቴራፒ - ባይኩስፒድ | እርስዎ $105 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| የሩት ካናል ቴራፒ - ሞላር | እርስዎ $130 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| ኦሲዮስ ቀዶ ጥገና (በእያንዳንዱ ኳድራንት) | እርስዎ $150 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| ሩት ፕላኒንግ (በእያንዳንዱ ኳድራንት) | እርስዎ $75 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **የአፍ ቀዶ ጥገና ሕክምና** | |
| መደበኛ ጥርስ ነቀላ (አንድ ጥርስ) | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| በቀዶ ጥገና ጥርስ ነቀላ | እርስዎ $100 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **የኦርቶዶንቲያ ጥርስ ሕክምና** | |
| ቅድመ የኦርቶዶንቲያ ጥርስ ሕክምና | እርስዎ $150 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ** |
| ሁሉን አቀፍ የኦርቶዶንቲያ ጥርስ ሕክምና | እርስዎ $2,500 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **ጥርስ ገጠማ** | |
| የጥርስ ገጠማ ቀዶ ጥገና | የጥርስ ገጠማ ጥቅማ ጥቅም ከፍተኛ $1,500 በቀን መቁጠሪያ አንድ ዓመት |
| **የተለያዩ ጉዳዮች** | |
| በቦታው ላይ የሚሰጥ ማደንዘዣ | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| የጥርስ ላብራቶሪ ክፍያዎች | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| ኒትሩስ ኦክሳይድ | እርስዎ $40 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| የስፔሻል ዶክተር ሕክምና ምርመራ | በእያንዳንዱ ምርመራ እርስዎ $30 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| ከአካባቢ ውጭ የተሰጠ ድንገተኛ ሕክምና ወጪን መልሶ መክፈል | ከ$250 በላይ ለሆነ ለሚመጡ ክፍያዎች እርስዎ ይከፍላሉ |

*TMJ ዓመታዊ ከፍተኛው $1000/ $5000 የዕድሜ ልክ ከፍተኛ አለው።
**ታካሚው የህክምና ዕቅዱን ከተቀበለ ለሁሉን አቀፍ ኦርቶዶንቲያ ሕክምና የጣምራ ክፍያ ይከፈላል።

## ተለይተው የሚቀሩ

ፕሮስቴቲክ ዕቃው ከተገጠመ በኋላ የመድን ሽፋኑ ካበቃ ከ60 ቀናት በላይ ከሆነው በርካታ የሕክምና ቀጠሮ ቀናትን ወይም ማስተካከያዎችን የሚጠይቁ ብሪጆች፣ ክራውኖች፣ ዴንቸሮች ወይም ፕሮስቴቲክ መሣሪያዎች።

ዓባሪ መሣሪያዎችን፣ ጥገና እና የጥርስ ተከላ ተዛማጅ አገልግሎቶችን ጨምሮ የጥርስ ተከላዎች የመድን ሽፋን ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን ቀደም ብለው የተጀመሩ ሕክምናዎችን ወይም አገልግሎቶችን ማጠናቀቂያ ወይም መስጫ።

ከመድን ሽፋኑ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን ቀደም ብለው የተሰጡ ኢንዶዶንቲክ አገልግሎቶች፣ ፕሮስቴቲክ አገልግሎቶች እና ጥርስ ተከላዎች። ከመድን ሽፋኑ ማብቂያ ቀን በኋላ ከ60 ቀናት በላይ ቆይቶ የተጠናቀቀ ኢንዶዶንቲክ ቴራፒ። የመድን ሽፋን ከሌለው አገልግሎት ጋር በተገናኘ በተለይ የሚደረጉ የሕክምና ምርመራዎች ወይም ምክክሮች። የሙከራ ወይም የምርምር አገልግሎቶች እና ተዛማጅ ምርመራዎች ወይም ምክክሮች።

ከክራውኖች፣ ብሪጆች ወይም የጥርስ ተከላዎች ጋር የሚደረግ የተራቀቀ ማስተካከያን ጨምሮ ወይም ማሸግን፣ ተቆልቋይ ዳይሜንሽንን መቀየር፣ ኦክሉሽንን ወደ ነበሩበት መመለስ ወይም መጣመምን፣ መጋጥን ወይም መሸርሸርን ማስተካከል ጨምሮ ሙሉ የአፍ እንደገና ማስተካከያ።

ለጥርስ የሕክምና ዘዴዎች፣ የሐኪም አገልግሎቶች ወይም ለተቋም ክፍያዎች ከጥርስ ሕክምና ማዕከሉ ውጪ በሆስፒታል በመተኛት የሚሰጥ ሕክምና። ማክሲሎፋሺያል ፕሮስቴቲክ አገልግሎቶች።

የሌሊት ጥርስ ምላስን እንዳይነክስ ማገጃ።

የግል ልዩ ማስተካከያ ሕክምናዎች።

በተለይ መልክን ለማሻሻል፣ ለመለወጥ ወይም ለማላቅ በዋንኛነት የታሰቡ የፕላስቲክ፣ ዳግም ማስተካከያ ወይም ኮስሞቴክ ቀዶ ጥገና እና ሌሎች አገልግሎቶች ወይም አቅርቦቶች።

የመድኃኒት ማዘዣ እና ያለ ሐኪም ትዕዛዝ የሚሸጡ መድኃኒቶች እና ቅድመ ሕክምና አገልግሎቶች።

ከ24 ሰዓት በቅድሚያ ከሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ውጭ ላመለጡ ቀጠሮዎች ወይም ለተሰረዙ ቀጠሮዎች አገልግሎት ሰጪው ክፍያ ሲያስከፍል።

የጠፉ፣ የታጡ ወይም የተሰረቁ ጥርስ ላይ የሚገጠሙ ነገሮች፤ በአግባቡ ካለመጠቀም፣ በአያያዝ ጉድለት ወይም ቸልተኝነት ለተበላሹ ጥርስ ላይ የሚገጠሙ ነገሮች መተኪያ።

የድምፅ ወደነበረበት ለመመለስ የሚደረግ ማስተካከያ።

በሐኪም በታዘዘው የሕክምና ዕቅድ እና/ወይም በ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም ያልተመከሩ እና ያልተፈቀዱ አገልግሎቶች እና ተዛማጅ ምርመራዎች ወይም ምክክሮች።

ካለው ተጨባጭ የጤና ችግር ምርመራ፣ እንክብካቤ ወይም ሕክምና ዓይን ሲታዩ አስፈላጊ የማይባሉ አገልግሎቶች እና ተዛማጅ ምርመራዎች ወይም ምክክሮች።

ፈቃድ ካለው የጥርስ ሐኪም፣ ዴንቱሪስት፣ ሃይጂኒስት ወይም የጥርስ ሕክምና ረዳት ውጭ ባለ በማናቸውም ሰው የሚሰጡ አገልግሎቶች።

በፕሮፌሽናል የአትሌቲክስ ውድድር ላይ በመሳተፍ ወይም በመወዳደር ወቅት ለደረሰ ጉዳት የሚሰጥ ሕክምና አገልግሎቶች።

በሠራተኛ በሥራ ቦታ ላይ የሚደርስ ጉዳት ካሣ ሥር የመድን ሽፋን ያላቸው ወይም የቀጣሪው ኃላፊነት የሆኑ አካል ጉዳቶች ወይም በሽታዎች ሕክምና አገልግሎቶች።

ሆን ተብሎ በገዛ ራስ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች ሕክምና የሚሰጡ አገልግሎቶች።

ሕግ የሚያስገድድ ካልሆነ በቀር የአገልግሎቱ የመድን ሽፋኑ በማናቸውም የፌደራል፣ የስቴት ወይም ሌላ የመንግሥት ፕሮግራም ሥር ሊገኝ የሚችል ሲሆን።

በውሉ ላይ ሽፋን እንዳላቸው ተድርገው ያልተዘረዘሩ አገልግሎቶች።

የመድን ሽፋን ካላቸው የመከላከያ አገልግሎቶች ውጪ የፓቶሎጂ፣ የዳይስፋንክሽን፣ ወይም በሽታ ማስረጃ የሌለው አገልግሎት ሲሆን።

## ገደቦች

አማራጭ አገልግሎቶች አንድን የጤና ችግር ለማከም ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ፣ በ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም የሚመከር አገልግሎት የመድን ሽፋን ይኖረዋል።

የጥርስን ተግባር የሚያሰናክሉ ኮንጀኒታል ወይም የዕድገት ብልሽቶች ለማስተካከል የሚሰጡ በውሉ ላይ የተዘረዘሩ አገልግሎቶች እና ደጋፊ መዋቅሮች የጥርስ ሕክምናው አስፈላጊነት ከተረጋገጠ ራሳቸውን ላላቻሉ ሕፃናት ሲሰጡ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል። የ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም በጥርስ ሕክምና ዓይን ሲታይ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን እና ኦርቶግናቲክ ቀዶ ጥገናው የኮንጀኒታል ወይም የዕድገት ብልሽት ላለበት ዕድሜው ከ19 ዓመት በታች ለሆነ ተመዝጋቢ እንዲደረግ ፈቃድ ከሰጠ በውሉ ላይ በተጠቀሰው መሠረት ኦርቶግናቲክ ቀዶ ጥገና የመድን ሽፋን ይኖረዋል።

ክራውኖች፣ ካስቶች ወይም ሌላ ቀጥተኛ ያልሆኑ የተፈበረኩ ማስተካከያዎች በጥርስ ሕክምና አስፈላጊ ከሆኑ ብቻ እና በ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም አስፈላጊ እንደሆኑ እና የሚመከሩ ሆነው ሲገኙ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል።

የመጀመሪያው የሩት ካናል ቴራፒው በ Willamette Dental Group ጥርስ ሐኪም የተጀመረ ከሆነ የሩት ካናል ቴራፒው ዳግመኛ ሕክምና ለመጀመሪያዎቹ 24 ወራት እንደ የመጀመሪያው ሕክምና አንድ አካል ተቆጥሮ የመድን ሽፋን ይኖረዋል። የመጀመሪያው የሩት ካናል ቴራፒው ተሳታፊ ባልሆነ አገልግሎት አቅራቢ ከተከናወነ፣ የዚህ ሩት ካናል ቴራፒው በ Willamette Dental Group ጥርስ ሐኪም ዳግመኛ ሕክምና ሲደረግለት ተገቢነት ያላቸው ጥምራ ክፍያ ግዴታዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

አጠቃላይ አንስቴዚያ በጥርስ ሕክምና ማዕከል ውስጥ የተከናወነ ከሆነ በውሉ ላይ በተጠቀሰው የጣምራ ክፍያ አከፋፈል አማካይነት የመድን ሽፋን ይኖረዋል፤ ይህ ሲሆን አገልግሎቱ የመድን ሽፋን ያለው ሲሆን እና የመድን ተመዝጋቢው ዕድሜው ከ7 ዓመት በታች ስለሆነ፣ የአካል ዕድገት ስንክልና ወይም አካለ ጉዳት ያለበት ስለሆነ በጥርስ ሕክምና ዓይን አንጻር ሲታይ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው።

በሕክምና አስፈላጊ ሆነው ከተገኙ፣ በ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም በቅድሚያ በጽሑፍ ፈቃድ የተሰጠባቸው ከሆኑ፣ የሚሰጡት አገልግሎቶች በጥርስ ሕክምና ማዕከል ከሚሰጡት ሕክምናዎች ጋር ተመሳሳይ ሕክምናዎች ከሆኑ እና ተገቢነት ያላቸው የጣምራ ክፍያ ክፍያዎች ከተከፈሉ በሆስፒታል ውስጥ በጥርስ ሐኪም የሚሰጡ አገልግሎቶች የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል።

ተጨማሪው ነገር ከተገጠመ 5 ዓመት ካለፈው እና የእርስዎን ጥቅማ ጥቅሞች ከፍ ያለ ደረጃ ለማድረስ ተጨማሪውን ነገር በሌላ መተካት በጥርስ ሕክምና ዓይን ሲታይ አስፈላጊ መሆኑ ከታመነበት ቀደም ሲል የነበረ ዴንቸር፣ ክራውን፣ ኢንሌይ፣ ወይም ሌላ ፕሮስቴቲክ ተጨማሪ ነገር የመድን ሽፋን ይኖረዋል።

የ Willamette የጥርስ ህክምና አቅራቢን ማየት አለብዎት።

# የተለመዱ የኢንሹራንስ ልዩ ቃላት

የእርስዎን የጤና ኢንሹራንስ ዕቅድ የበለጠ ለመረዳት አንዳንድ የተለመዱ የኢንሹራንስ ቃላትን ትርጓሜ ይማሩ።

### ጣምራ ኢንሹራንስ

ጣምራ-ኢንሹራንስ የእርስዎን ተቀናሽ (የእርስዎ የመድን ዕቅድ ያለው ከሆነ) ካሟሉ በኋላ ለሕክምና አገልግሎቶች እርስዎ የሚከፍሉት ገንዘብ መቶኛ ነው።

### ጣምራ ክፍያ

ጣምራ ክፍያ በዶክተር ለመታየት፣ ለድንገተኛ ሕክምና ክፍል ሕክምና እና ብዙውን ጊዜ በሐኪም ለሚታዘዙ መድኃኒቶች እርስዎ የሚከፍሉት ገንዘብ መጠን ነው። አንዳንድ የመድን ዕቅዶች ተቀናሾችን ከማሟላት ይልቅ ጣምራ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ያስገድድዎታል። ሌሎች የመድን ዕቅዶች ሁለቱንም እንዲያደርጉ ሊያስገድዱ ይችላሉ። የእርስዎ ጣምራ ክፍያዎች በተቀናሹ ገንዘብ መጠን ላይ ታሳቢ አይሆኑም ሆኖም ግን በእርስዎ ከኪስ ወጪ ተከፍሎ የሚደረግ ገንዘብ ገደብ ላይ የሚታሰቡ ይሆናሉ።

### የጣምራ-ፕሪሚየም/ፕሪሚየም

የአርቦን (ፕሪሚየም) በየወሩ የጤና ሽፋንዎ ሙሉ ወጪ ነው። የጣምራ-ፕሪሚየም እርስዎ የሚከፍሉት የጠቅላላ የጤና ሽፋንዎ መቶኛ ወይም የተወሰነ መጠን ነው። ለምሳሌ፦ ለግል ሽፋንዎ ያለው ትብብር በወር $25 ብቻ ነው። ሆኖም ግን፣ በሽፋን ውስጥ ጥገኞችን ለመመዝገብ ከመረጡ፣ የእርስዎ ወርሃዊ የጣምራ-ፕሪሚየም ከፍ ያለ ይሆናል። ለወጪዎች ገጽ 4ን ይመልከቱ።

### ተቀናሽ

ተቀናሽ የእርስዎ የመድን ሽፋን ዕቅድ መክፈል ከመጀመሩ በፊት የመድን ሽፋን ላላቸው የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች የመድን ሽፋን ባለው ክፍለ ጊዜ (ብዙውን ጊዜ አንድ ዓመት) ወቅት እርስዎ የሚከፍሉት ገንዘብ ነው። ተቀናሹ በሁሉም አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚ ላይሆን ይችላል እና ሁሉም የመድን ዕቅዶችም ተቀናሽ የላቸውም። ለአንዳንድ የመድን ዕቅዶች፣ ተቀናሹ ከአውታረ መረብ ውጭ ላሉ አገልግሎቶች ብቻ ተፈጻሚ የሚሆን ነው።

### ጥገኛ

ጥገኞች በSEIU 775 Benefits Group በኩል በዕቅድዎ ላይ የመድን ሽፋን ለማግኘት ብቁ የሆነ ልጅ (እስከ 26ኛ ልደታቸው ድረስ) ነው። ብቁ ጥገኞችን ዝርዝር ለማግኘት **myseiu.be/oe-dv-22** ን ይጎብኙ።

### ብቁነት

በተከታታይ ለሁለት ወራት ለ 80 ሰዓታት በወር በትንሹ ከሠሩ በ SEIU 775 Benefits Group የግል የጤና የመድን ሽፋን ለማግኘት ብቁ ነዎት። በእርስዎ የመድን ሽፋን ብቁ እንደሆኑ ለመቆየት፣ በወር 80 ሰዓታት መሥራትዎን መቀጠል መቻል አለብዎት። በወር 120 ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ ከሰሩ ጥገኛ(ችዎን) በ $10 የጥርስ ህክምና ለመመዝገብ ብቁ ነዎት።

### አውታረ መረብ ውስጥ ያለ እና ከአውታረ መረብ ውጭ ያለ ልዩነት

በአውታረ መረብ ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች የእርስዎ የጤና መድን ዕቅድ ሽፋን የሚሰጣቸው እና በዝቅተኛ ወይም ያለ ምንም የጣምራ ክፍያ/ጣምራ ኢንሹራንስ ሊያገኙዋቸው የሚችሏቸው አገልግሎቶች ናቸው። ከአውታረ መረብ ውጭ ያሉ አገልግሎቶች አሁን በእርስዎ የመድን ዕቅድ የሚሸፈኑ ሊሆኑ ወይም ላይሆኑ ይችላል ሆኖም ግን ከአውታረ መረብ ውስጥ ካሉ አገልግሎቶች ይልቅ ከፍተኛ ጣምራ ክፍያ ወይም ጣምራ ኢንሹራንስ ሊኖራቸው ይችላል።

### የአባል መታወቂያ

የእርስዎ የአባል መታወቂያ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች እና ሠራተኞቻቸው የእርስዎን የመድን ሽፍን ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ እና ለአገልግሎቶቹ ክፍያን ማስተካከል እንዲችሉ የሚያግዛቸው ልዩ ከእርስዎ ጋር የተገናኘ ቁጥር ነው። እንዲሁም የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች የተወሰኑ አባላትን ለማግኘት የሚጠቀሙበት ቁጥር ነው። የእርስዎ የአባል መታወቂያ ቁጥር በእርስዎ የአባል መታወቂያ ካርድ ላይ ሊገኝ ይችላል።

### አውታረ መረብ

የእርስዎ የጤና መድን የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ ከእነርሱ ጋር ውል ያለው አውታረ መረብ የተቋማት፣ የአገልግሎት ሰጪዎች (ዶክተሮች፣ ነርሶች) እና አቅራቢዎች ስብስብ ነው።

### ከኪስ የሚከፈል ገንዘብ ገደብ

ከኪስ የሚከፈል ገንዘብ ገደብ የእርስዎ የመድን ዕቅድ ለተቀረው የዓመቱ ክፍለ ጊዜ የመድን ሽፋን ላላቸው የጤና ወጪዎች 100% መክፈል ከመጀመሩ በፊት እርስዎ መክፈል ያለብዎት ገንዘብ መጠን ነው። በአጠቃላይ አነጋገር፣ ጣምራ ክፍያዎች፣ የእርስዎ ተቀናሽ፣ ጣምራ ኢንሹራንስ እና የመድን ሽፋን ያላቸው የአውታረ መረብ ውስጥ ክፍያዎች በዚህ ገደብ ላይ ታሳቢ ይሆናሉ።



Dora P.
ተንከባካቢ፣ Tacoma

### ተቀዳሚ የሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ወይም አገልግሎት ሰጪ (ዶክተር)

ተቀዳሚ የሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ለተከታታይ ሕክምና እርስዎን የሚያይዎት እንደ ነርስ ወይም ሐኪም ረዳት፣ ዶክተር ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ነው። የእርስዎን ተቀዳሚ እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ በእርስዎ የጤና መድን ዕቅድ የድር ጣቢያ በኩል መምረጥ ይችላሉ። አንዳንድ የመድን ዕቅዶች ራሳቸው አንዱን ሊመድቡልዎት ይችሉ ይሆናል፣ ሆኖም ግን በማናቸውም ጊዜ ሊለውጡት ይችላሉ።

### የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች እና የተኝቶ ታካሚ አገልግሎቶች

ተኝቶ ታካሚ አገልግሎት ለአንድ ሌሊትም ቢሆን በሆስፒታል ወይም በህክምና ተቋም ውስጥ እንዲያድሩ የሚያስገድድዎት ሕክምና ነው። አንዳንድ ምሳሌዎች ሕፃን መውለድ ወይም አንዳንድ የቀዶ ጥገና ሕክምናዎች ናቸው። የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎት ማናቸውም በሆስፒታል ወይም በህክምና ተቋም ውስጥ እንዲያድሩ የማያስገድድዎት የሕክምና አገልግሎት ነው።

### ይለፈኝ ማለት ወይም የይለፈኝ የመድን ሽፋን

በጤና መድን ሽፋን መመዝገብ ካልፈለጉ ወይም ለእርስዎ ወይም ለጥገኛ(ዎችዎ) (ከተመዘገቡ) ሽፋንን ማቆም ከፈለጉ፣የወረቀት ቅፅ ለማግኘት Health: My Plan ላይ የሚገኘውን የኦንላይን ቅጽ መሙላት ወይም ወደ ደንበኛ አገልግሎት መደወል ይችላሉ። የመድን ሽፋኑን ለመተው ከመረጡ፣ እስከሚቀጥለው Open Enrollment (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን) (በየአመቱ ከጁላይ 1-20) ድረስ ወይም ብቁ የሆነ የህይወት ክስተት እስከሚኖርዎት ድረስ እንደገና መመዝገብ አይችሉም።

SEIU 775 BENEFITS GROUP






## ምዝገባ ክፍት የሚሆነው፡- ጁላይ 1 – ጁላይ 20

በHealth: My Plan ላይ ይመዝገቡ ወይም በእርስዎ የመድን ሽፋን ላይ ኦንላይን ለውጦችን ያድርጉ!

**myseiu.be/oe-myplan-22**

ጥያቄዎች አሉዎት?
ይደውሉ **1-877-606-6705**